በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዮት

The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ethiopian Biodiversity Institute

ቁጥር: ኢብሕኢ-100/3659/2014

ቀን: 02 ግንቦት 2014

ለሚመለከተው ሁሉ

ጉዳዩ:- **በአርክቦት ውል የተገኘ ገንዘብ አስተዳደርና አጠቃቀም ረቂቅ መመሪያ ላይ አስተያየት እንድትሰጡ ስለመጠየቅ**

ሀገራችን ኢትዮጵያ የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦት እና የማህበረሰብ መብቶች አዋጅ ቁጥር 482/1998 እና የሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 169/2001 አውጥታ ተግባራዊ እደረገች ትገኛለች። የዚህ አዋጅ ዓላማ የሀገሪቱ የጀነቲክ ሀብት እና ተያያዥ የማህበረሰብ ዕውቀትጥቅም ላይ በመዋሉ ከሚገኘው ጥቅም ሀገሪቱና ማኅበረሰቦቿ ፍትኃና ሚዛናዊ የሆነ ድርሻ እንዲያገኙ በማድረግ የብዝሀ ሕይወት ሀብት እንዲጠበቅና በዘላቂነት ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ ነው። በአዋጁ አንቀጽ 9(2) መሠረት በአርክቦት ውል መሠረት ከጀነቲክ ሀብት አጠቃቀም የሚገኝን በገንዘብ መንግሥትና የአካባቢ ማህበረሰቦች እኩል እንደሚጋሩ ይደነግጋል።

መንግስት በገንዘብ መልክ ከሚያገኘውን ጥቅም የጀነቲክ ሀብትን ለመንከባከብና ለማበልግ እና የማህበረሰብ ዕውቀትን ለማስፋፋት ተግባር እንደሚውል እና ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ኢንስቲትዩቱ ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ሊያወጣ እንደሚገባ የአዋጁ አንቀጽ 18(2) ይደነግጋል። በሌላ በኩል ከላይ በተጠቀሰው ደንብ አንቀጽ 30 እና 31 መሠረት ለማህበረሰቦች ጥቅም እንዲውል የተወሰነው የአርክቦት ገንዘብ የዚያ የጀነቲክ ሀብት ባለቤት ለሆነው ማህበረሰብ ጠቀሜታ ለሚነደፉ የልማት ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚ እንደሚውልና ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ኢንስቲትዩቱ የልማት ፕሮጀክት ኃሳቦችን በመቅረጽ ለሚመለከተው ለወረዳ፣ ለዞን፣ ለክልል እና/ወይም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በማቅረብ እንደሚያስወስን ተደንግጓል። በዚህ መሠረት ኢንስቲትዩቱ እነዚህን ተግባራት ለማከናወን ከላይ በተጠቀሰው አዋጅ አንቀጽ 18(2) እና ደንብ አንቀጽ 35(1) መሠረት "በአርክቦት ውል የተገኘ ገንዘብ አስተዳደርና አጠቃቀም መመሪያ" ረቂቅ ሰነድ አዘጋጅቷል።

ስልክ: +251-116-615607 Tele. +251-116-614145 +251-116-612244
ፋክስ : +251-116-613722 Fax +251-116-612542
ድህረ-ገጽ: www.ebi.gov.et Website:
ኢሜይል: info@ebi.gov.et E-mail:
ፖ.ሳ.ቁ: 30726 P.O.Box

Please quote our reference number when you reply

ስለሆነም ይህ መመሪያ ከመጽደቁ በፊት የባለድርሻ አካላትን አስተያየት ማካተት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በረቂቅ መመሪያው ላይ ያላችሁን አስተያየት እስከ ግንቦት 15 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ በጽሁፍ በማድረግ ለኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት በኢሜይል (email: fikirghion80@gmail.com) ወይም በአካል በመቅረብ በኢንስቲትዩቱ ጀነቲክ ሀብት አርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት ዳይሬክቶሬት እንድትልኩልን ወይም እንድትሰጡን እንጠይቃለን።

ከሠላምታ ጋር

ፈለቀ ወልደየስ ጋሞ (ዶ/ር)
ምክትል ዋና ዳይሬክተር
Feleke Woldeyes Gamo (PhD)
Deputy Director General

ግልባጭ፡-

- ለዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት
- ለምክትል ዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት
- ለጀነቲክ ሀብት አርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት ዳይሬክቶሬት

ኢ.ብ.ሕ.ኢ.